# ይድረስ ለቬሮኒሪካ መላኩ ተብዬ አጁማጃ

<<ያዝ እንግዲህ አዲስ አበቤ! >> በተሰኘ ርእስ www.zehabesha.com/amharic/?p=78079 የጻፍሽውን አንብቤ ምላሹን ጽፌልሻለሁ።

የአዲስ አበባን ነዋሪ ሕዝብን "እስኪ የተጭያነብህን ግብር ሰበብ አድርገን እኛም ደህና አድርገን በነገር እንጭያንህ" እያልሽ ምድር ለቀሽ ስትንበላጠጪ "ሰሞኑን አዲስ አበቤ ማንባት፣ ማላዘን፣ ምሬት አብዝቷል። ይህ ማላዘንና ቁጭት ከተማቸው በልዩ አዋጅ ሰብብ በመሸጧ እና አገር አልባ በመሆናቸው መስሎኝ ነበር።" በማለት ቀልበ ጮሬዋ መናጢ ሞጥሚጣ ስትቀላምጅ ቆይተሽ እራስሽን ደግሞ ያዲስ አበባ ተወላጅ እንደሆንሽ ለማስመሰል ብዙ ቀዣበረሻል። ከተማችን አዲስ አበባ እንዳንቺ ያለውን የወያኔዎች ማደጎ ሾካካ አታፈራም። ለማያውቁሽ ታጠኝ እንዲሉ በትክክል ስለምናውቅሽ ዝም ብለሽ ተደንሸሪ።

እዚያው የለመድሹውን ስለ "ዐማራ ብሔር፣ ብሔረሰብ" እያልሽ አላዝኝ፣ ቆዝሚ፣ እንደ በቀቀን አነብንቢ። አንቺና ብጤዎችሽ ያማራ ብሔር፣ ያማራ ብሔረተኛነት፣ ኅሠኛነትና ጽንፈኛነት እያለችሁ ጠዋት ማታ አልቃሾችና ጥሩንባ ነፊ ቡከን ስደተኛ ጉጀሌዎች ይህን በጣም ቦርቃቃ አፋችሁን ብትዘጉት ይሻላችኋል።።
ያማራውን ማኅበረስብ የኢትዮጵያዊ ብሔረተኛነት አቋምና እይታ ለማስቀየር እንዳበደ ውሻ ትሯሯርጣላችሁ። የኅብረተሰ እድገት ሂደትን የኋሊት ቀይራችሁ ዐማራውን ማኅበረስብ ወደ ጠባብ የጎሣ፣ የዝውግ ከረጢት ዝቅተኛ ደረጃ ለማዝቀጥ ቋምጣችኋል። ስለሆነም ነው ያማራ ጎሣኛነት ይለምልም እያላችሁ በአሜሪካና አውሮፓ በሩቅ ተወሽቃችሁ ቡራ ከረዩ የምትሉት።

ያዲስ አበባን ሕዝብ ለቀቅ አድርጉት። በናንተ የከሰረ ፖለቲካ የጎሣ ከረጢት ውስጥ ፈጽሞ አይገባላችሁም። በመሆኑም እንጥላችሁ ይውርድ። ማንም ቅጥረኛ ማወቅ ያለበት ዐቢይ ጉዳይ ዐማራው ማኅበረ ሰብ ከላይኛው ሰገነቱ ጭያፍና ከሰፊው ውቅያኖስ ኢትዮጵያዊ ማንነቱ ወርዶ በጎሣ ኩሬ ገብቶ የማይንቦጭያረቅ መሆኑን ነው።
ጀግናው አዲስ አበቤማ የጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎችና የቅጥረኞ የጎሣ ፖለቲካ አራማጆች ልዩ ይላማ የተደርገውና የሚሰደበው እኮ እምቢ ለወያኔ ትግሬ ሕወሓትና ለተለጣፊው የሆዳም ዐማሮች ጥርቅም ብአዴን ተብዬው የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣና የዘር ፖለቲካ በማለቱ ነው።

በነገራችን ላይ ወያኔ ትግሬ ሕወሓትን፣ አቅፈው ደግፍፈው፣ ስንቅና ትጥቅ አቅርበው ዘመቻ ቴዎድሮስ በሚሉት ሸዋ ተወሮ አዲስ አበባ አራት ኪሎ ላይ ፀረ ኢትዮጵያ ቅጥረኞቹ እነ መለሰ (ለገሠ) ዜናዊ፤ የአድዋው የባንዳው ውላጅና ታምራት ላይኔ ተብዬው የሰቆጣ ተወላጅ ነኝ ባይ ሶለግ ውሻና የሱካር ሌባ አጋሚዶ ለሥልጣን ያበቃችሁት የጎንደር፣ የጎጃምና የወሎ ዐማራ ተብዬዎች መሆናችሁን ምነው ቬሮኒካ ሽምጥጥ አድርገሽ አዲስ አበባዎችን "አህያ" እያልሽ ታሞጠሙጣለሽ። ጀግናው የሸዋ አምቦና የተጉለት ሰላድንጋይ ሕዝብ የወያኔንና የኢሕዴን የወሎኛ ጎንደር ገበሬ ጦር በገፍ ሲመነጥረው ታምራት ላይኔ በራዲዎ ቀርቦ ሲያለቅስ አልነበረም?
የሐረር ከተማ ሕዝብ ከተማዋን በወያኔ ላለማሲያዝ ደንጎጎ ላይ ለሳምንታት በጅግንነት ተዋግቶ የነታምራትን ላይኔን ገበሬ ሠራዊት ድባቅ ስለመታው ነው በሐረርጌ የዐማራውን ማኅበርሰብ ላይ ለይቶ የእልቂት ዘመቻውን ያስጀመረው።
እራሱን ኢሕዴን ከማለት ወደ በአዴን የቀየረው የትግሬ ሕወሓት ወደል አህያ ነው ዐማራውን ኢትዮጵያዊ ማኅብረስብ ያስጨፈጨፈው፣ የሚያፈናቅለው። ብአዴን ወያኔ ትግሬ ከሰጠው ያማራ ክልል ውጪ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በሐረርጌ ወዘተረፈ ፈጽሞ በማያገባው ነገር በተለይም ሰሞኑን በአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ላይ ከወያኔ ሕወሓትና ኦህዴድ ጋራ ሴራ ይሸርባል።
ወያኔ ትግሬ ሕወሓትና ብአዴን ተብዬዎቹ ወራሪ ዘራፊዎች እንጂ ያዲስ አበበባ ነዋሪ ሕዝብ በዲሞክራሲያዊ ውክልና ድምፁን የሰጣቸው አይደሉም።

ማንም ማወቅ ያለበት ሐቅ አለ። ይህም የወያኔ ትግሬና ሁሉም ጀሌዎች፣ ልዩ አዋጅና የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ሕገ መንግሥት በምንም ዓይነት በመላው ኢትዮጵያ ተቀባይነት የለውም። አዲስ አበባ ከሁሉ በተቀዳሚ የሸዋ ዋና ከተማ ናት። ከሸዋ ነባር ነዋሪ ሕዝብ በስተቀር መጤ የወያኔ ትግሬና፣ የትግሬ-ዐማራ ብአዴን ከአዲስ አበባ ተለቃቅመው ወደ መጡበት ወደው ሳይሆን ተገደው ይባረራሉ። ያዲስ አበባ ነባር ነዋሪ የሸዋ ተወላጆች ብቻ ናቸው። የወለጋ፣ ያሩሲ፣ የጅማ፤ የአሩስ፣ ወዘተረፈ ወረሞ ጎሣዎች ስለ አዲስ አበባ ከተማ አያገባቸውም። ማንም ጎሣ የተለዬ ጥቅም በአዲስ አበባ ላይ የለውም። የኦነግ፤ የሕወሓትና ሻዕቢያ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ይከሽፋል።

ያዲስ አበባ ከተማ በታሪካዊው ጥንታዊ የመናገሻ አውራጃ ውስጥ ባራቱም አቅጣጭያ መስፋት ትችላለች። ለዚህም የማንንም ፈቃድና ሰጭነት አትጠይቅም። በወራሪው ፋሽስት ቅጥረኛ ወያኔ ትግሬ ሕወሓት መቃብር ላይ ነጻ የሸዋ መንግሥት ይመሠረታል። ያዲስ አበባ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብትና ነፃነቱ ይረጋገጣል።

ያዲስ አበባ ጀግና ሕዝብ ወያኔ ትግሬንና ግብረ አበሮቹን እነ ብአዴን የተባሉት የሆዳማ አሳማ ዐማራ ተብዬ የጎንደር፣ የጎጃምና የወሎ በጣም ወራዳ የስኳር ሌቦችንና ሙሰኞች ጥርቃሞ፤ የወያኔ ማደጎ አሽከር ተላላኪ ወረሞዎች፤ እራሳቸውን ኦሕዴድ ባይ የስግብግብ ካድሬዎች ክምችቶችን በዲሞክራሲያዊ ነጻ ምርጭያ ጠራርጎ በማባረሩ ነው በጠራራ ፀሐይ የተጨፈጨፈው።

እረ! ለመሆኑ ያዲስ አበባ ሕዝብ በወያኔ ትግሬ አጋዚ ልዩ ቅልብ ጦር በገፍ የአዲስ አበባ ሕዝብ በዳግማዊ ግራዚያኒ ጥቁር ፋሽስት ወያኔ ትግሬዎች ሲጨፈጨፍ የጎጃም፣ የጎንደርና የወሎ ከተማና ገጠር ነዋሪ ሕዝብ የት ነበር?

የወያኔ ትግሬ ጌሾ ወቃጭና ቅራሬ አጭያላጭ ሁሉ አዲስ አበባ እየተመላለስ የግል ጥቅመኛ የሆናችሁ በሸዋ አዲስ አበባ ሕዝቡ ኪሳራና ድህነት ለማትርፍ ላይ ታች ታሽቃብጣላችሁ። አደብ ግዙ።

ቬሮኒካ ተብዬዋ የወያኔ ደንገጡር እንደ ባልትናየለሽ ሴት ያልፈላ ሹሮ ዘወትር ያማራ ብሔርና ብሔረተኛነት እያለች የምትንደከደከው በምን ሂሳብ ነው የሸዋ አዲስ አበባ ነዋሪን "እንደ አህያ ግፍ መሸከም አይሰለችህም" እያለች የምትፎልለው?የወያኔ ትግሬን የግፍ ቀንበር ተሸክሞ በጣም ሲበዛ ወገቡ የጎበጠው የጎጃም፣ የጎንደርና የወሎ ዐማራ ክልል ተብዬ ነዋሪ ነው። ጎንደር ሆነ ጎጃም በወያኔ አግአዚ አልሞ ትኳሽ ከተጨፈጨፈ በኋላ በጦር አዋጅ ሥር ገብቶ ጸጥ ብሏል እንጂ ወራሪውንና ተስፋፊውን ወያኔ ትግሬን ከተከዜ ማዶ አባሮ ነፃነቱን ሲቀዳጅ አላየንም። ያማራ ጎሣ ብሔረተኛነትና ጽንፈኛነት ወሬ አቃላጮች አንድም እሥረኛ፣ አንድም ትንሽ መንደር ይሁን ከተማ በጎንደር ሆነ በጎጃም ከወያኔ ትግሬ ቅኝገዥነት ነፃ ያደረጉት የለም።

በወያኔ ትግሬ ሕወሓትና ጀሌዎቹ ከፍተኛ ኢክኖሚያዊ፣ ፖለቲካና ማኅበረሰባዊ ችግር ከደረሰባቸው ከተሞች በግንባር ቀደም ደረጃ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ይገኛሉ።

ውክልና የሌለው ያዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ በገፍ ከመኖሪያ ቤቱ ይፍናቀላል፡ ከፍተኛ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል። ዶማ ሰቀል መጤዎች በከተማዋ ውስጥ በብርሃን ፍጥነት ከብረው ሲንደላቀቁ ነዋሪ ግን ከዓመት ወደ ዓመት በከፍተኛ የኑሮ ውድነት ለችጋርና ጉስቁልና ተዳርጓል።

ቬሮኒካ የሰሞኑን ወያኔ ትግሬና ኦሕዴድ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የሚያደርጉትን የቀን ገቢ ግብር ተመና አስመልክታ በንጽጽር የጎጃም ገበሬ በንጉሡ ዘመን የትምህርትና የጤና ታክስ ክፈል ሲባል አልከፍልም ብሎ አመጽ ማድረጉን ጠቅሳለች። የጎጃም ገብሬዎችን አመጽ ለማመስገን ስለምን የአዲስ አበባን ነዋሪ መስደብ አስፍለጋት?

የኢትዮጵያ ገበሬዎች ለልጆቻቸው ትምህርት ቤት፣ ለጤናቸው ሐኪም ቤት እንዲገነባላቸው ግብር የመክፍል ግዴታ ነበረባቸው። ኢትዮጵያ በንጉሡ ዘመን ምንም እዳ አልነበረባትም። ዛሬ በዘመነ ወያኔ ትግሬ የኢትዮጵያ መንግሥት ተብዬ እዳ ከ 22 ቢሊዎን ዶላር በላይ እንደሆነ ይታወቃል። አገሩም ሕዝቡም ተሸጧል። በአንድ በኩል ጎጃም፣ ጎንደር፣ ወሎ ኋላቀር ክፍለ ሀገራት ነበሩ እየተብለ ይቦተለካል፣ በሌላ በኩል ግብር አለመክፈል ጀግንነት ተድርጎ ይተረካል።

ደርቤ በላቸው ቀጀላ    አባ ስግምግም
ከየካ ክፍለ ከተማ
አዲስ አበባ